# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ** 35 **ቁጥር** 1 **መስከረም** 2002 **ዓ.ም.**


## <u>አዲሱን ዓመት በቀጣይ ትግል እናጅበው!!</u>

*የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተገባድዶ የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከሀገራችን ከተባረረ ይኸው ስድሳ ዘጠኝ ዓመት ሆነው። በእነኝህ ሰድሳ ዘጠኝ ዓመታት በሀገራችን ኢትዮጵያ ሦስት አምባገነን ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል። ሦስቱም በሕዝብ ያልተመረጡ፥ ለሕዝብ ያልቆሙና ለሕዝብ ያልመጡ በመሆናቸው፥ አምባገነንነታቸው የማይጠበቅ አይሆንም። ከዚሁ የዓለም ጦርነት ፍፃሜም በኋላ ከሀገራችን የተባረረው የቅኝ ግዛት ወራሪ ኃይልም እንደዚሁ በበኩሉ፥ ሕዝብ ፈጅቶ፥ ሀገር አውድሞ፥ ሀብት ንብረት ዘርፎ፥ ሰማዕታት አርበኞቻችንን ጨፍጭፎ ቢሄድ የሚያስገርም አልነበረም - አመጣጡ ለዚሁ ነበርና! በእነኝህ ስድሳ ዘጠኝ ዓመታት በዓለም ውስጥ ከፍተኛ የሆኑ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊ፥ ዕድገት ለውጦች ተካሂደዋል። ከመቶ በላይ የቅኝ ግዛት ሀገሮች ከባርነት ቀንበር በመላቀቃቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ነፃነታቸውን ተጎናጽፈዋል። ቀሪው የዓለም ክፍል በትምህርት፥ በሳይንስ ምርምር፥ በቴክኒየሎጅ ጥበብ፥ በሀብት ክምችት፥ በልማት ዕድገት አስገራሚ ዕመርታን አሳይቷል። በአብዛኛው የዓለም ክፍል የሚኖረው ሕዝብ፥ ከሞላ ጎደል የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል ጥረት ግረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ትላንት በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ በርካታ ሀገሮች ዛሬ በሁለንተናዊ የልማት መስፈርት መመዘኛ አንደኛው ዓለም ከሚባለው ደረጃ የሚመደቡ ናቸው። ቻይና፥ ሕንድና ፓኪስታን ዛሬ የኒውክለር መሳሪያ ባለቤቶች ሆነዋል። ዜጎቻቸውን መግበውና አልብሰው የሚኖሩ ሀገሮች በርካታ ናቸው። እንደ ኢትዮጵያ በጣት ከሚቆጠሩ ያልታደሉ ሀገሮች ካልሆኑ በስተቀር አብዛኛዎቹ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች በዕድገት ብሩኅ ተስፋ ሂደት ውስጥ ይገኛሉ። እንደ ጃፓን፥ ሕንድና ቻይና የመሳሰሉ ነባርና ጥንታውያን ተብለው የተፈረጁ ሀገሮች፥ በአጭር ጊዜ ከተኣምራዊ የዕድገት ደረጃ መድረሳቸው እንደ መልካም አርዓያ ተቆጥሮላቸዋል። በዚህም የተነሳ በአለፉት ስድሳ ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ እንደኢትዮጵያ የኋልዮሽ በመሄድ አድሮ ጥጃ የሆኑ ሀገሮች አሉ ብለን ማመን ቸግሮናል ።*

*ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍፃሜ ማግሥት፥ ብዙ ሀገሮች የተለያዩ ለውጦችን አይተዋል። የበርካታ አምባገነን ጭቆና መሣሪያ የነበረ የአንድ ብቸኛ ፓርቲ ሥርዓት ተደምስሷል። ሁሉም አምባገነን*

ገዥዎች ወደማይቀርላቸው ከርሰ-መቃብር ወርደዋል። በሰው-ሰራሽ ልዩነት ምክንያት ተለያይተው የነበሩ ሀገሮች እንደገና ተዋህደዋል። ቤተሰቦች ተገናኝተዋል። ለዚህም፥ የጀርመንና የየመን ሕዝቦች እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ሆነዋል። ለአለፉት ሃያ ዓመታት፥ እንደየሀገሮቹ ሕዝቦች ፍላጎት፥ ምኞትና ውሳኔ የየበኩላቸውን ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ እያካሄዱ የየራሳቸውን መንግሥት በመቋቋም እንደየፍላጎታቸው በዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ ይገኛሉ። እንደየዜጎቻቸው ችሎታና አቅም ከሞላ ጎደል የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይታያሉ። ሌላው ቢቀር፥ በስንት መሥዋዕትና ትግል ያገኙትን ነፃነትና ሀገራዊ ልዕልና አስከብሮ ለመጠበቅ የሚችሉ ብሔራዊ መንግሥታት አሏቸው። ሁሉም በዜግነቱ የሚኮራ እንጂ የሚያፍርና የሚከዳ መንግሥት የላቸውም። ብዙዎች መንግሥታት፥ የብሔራዊ ጥቅምን፥ የግዛት ልዕልናን፥ የዜጎች እኩልነትንና አንድነትን፥ ሀገራዊ ነፃነትንና ዳር ድንበርን ጠብቀው የሚያስጠብቁ ናቸው። አሳዛኝና አሳፋሪነቱ ከቀዝቃዛው ጦርነት ወዲህ በኢትዮጵያ የተደረገው ሂደት ግን የዚህ ተቃራኒ መሆኑ ነው። በመሆኑም፥ የቀዝቃዛው ጦርነት ፍፃሜ ለኢትዮጵያ መጣባት እንጅ፥ አልመጣላትም የሚባለው ከዕውነት የራቀ ነው አይባልም። ምክንያቱም፥ በሀገራችን ሰው-በላ አምባገነን ሄዶ፥ የተተካው ሀገር-በላ ዘረኛ ሥርዓት በመሆኑ ብቻ አይደለም። ጭቆናንና ምዝበራን አስወግደን፥ የዜግነት መብታችን በማስከበር በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረን መኖራችንን እንቀጥል የሚሉቱን ዜጎች፥ ተገነጣጥላችሁ ተበተኑ የሚል ሕግ አውጥቶባቸው እንዲኖሩ በመገዳደቸውም ጭምር ነው። ዳር ድንበር ማስከበሩ ቀርቶ፥ የሀገርን መሬት ለባዕድ መንግሥት የሚሸጥ ሥርዓት በመተከሉ፥ ለኢትዮጵያ የቆመ ኢትዮጵያዊ መንግሥትን ለማምጣት የሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የትግሉን ውጤት የሚያይበት አዲስ ዓመት ለማክበር ዛሬ እየከፈለ ያለው መሥዋዕት የነገን ብሩኅ ተስፋ አብሳሪ የነፃነት ደወል ነው ብለን እናምናለን። በዘረኞች ዳፍንት የወደቀችውን የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ወደ ብሩኅ ተስፋ ለመሸጋገር የምትታገለዋን የነገዋን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የበኩላችንን ግዴታ ለመወጣት፥ ያለን ምርጫ ትግላችንን በአዲሱ ዓመት ወደ አዲስ ምዕራፍ ማሸጋገር ብቻ ነው። ሌላ ምርጫ ሊኖረን አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የአዲሱ ዓመት ምኞትና ተስፋ፥ ሠላምና ፀጥታ፥ ደስታና ሀሴት፥ አንድነትና የጋራ ብልጽግና ቢሆንም እነኝህ ሁሉ ምኞቶች ግን እያደሩ የምድረ-በዳ ጥብርብር (ሚራጅ) ሆነውበት ቀርተዋል።

ይህን የ2002 ዓም አዲስ ዓመት በዓላችንን ስናከብር፥ ባኅላችን ነውና፥ "ያለፈው መከራ፥ የሚመጣው ደስታ ይሁንልን" እያልን የተስፋን ምኞት ተስፋ እንመኛለን። የሰው ልጅ በተስፋ ለመኖር ተስፋ የሚያደርገውን ምኞት ለመመኘት የሚፈልገው፥ የሰብዓዊ ተፈጥሮው ባኅርዩ ስለሆነ ነው። በመሆኑም ይህን የመስከረምን ወር የምናከበረው ከክረምት ወደ በጋ የሚያሸጋግረን የዘመን ወለወጫ ወቅት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ኅልውናዋ አደጋ ላይ የወደቀችውን ሀገራችንን ለማዳን አዲስ የትግል ጥሪ ለሕዝባችንና ወያኔን ተቃወሞ ለቆመው የአንድነት ኃራ እያስተላልፍን ነው። አዲሱን ዘመን ስንቀበል፥ ቂጠማ ጎዝጉዘን፥ አበባ ቀንጥሰን፥ ድግስ ደግሰን፥ ሕዝብ አሳትፈን፥ ነፃነትን

አክብረን፥ የዜጎቻችንን ምኞት አስፈፅመን፥ የሀገራችንን ሉዓላዊነት አስረግጠን፥ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አስጠብቀን፥ የሕዝባቻችንን እኩልነትና አንድነት አስከብረን ቢሆን ኖሮ፥ የአዲሱ ዓመት በዓላችን ዕጥፍ ድርብ በሆነልን ነበር፡፡ ደስታችንም ከአድማስ በላይ በሆነልን ነበር፡፡ ይህ ግን የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ ወደ ነገዋ ኢትዮጵያ እስካልተለወጠች ድረስ የሚሆን አይሆንም፡፡ በዚህ በአዲሱ ዘመን መለወጫ በዓል፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ስለ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ ምንነትና ሁኔታ ለመዘርዘር አንቃጣም፡፡ ምክንያቱም፥ ዜጋዋ፥ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ እየኖረባት ብቻ ሳይሆን እየሞተባትም፥ እያዘነላት ብቻ ሳይሆን እያዘነባት፥ እየተደሰተባት ሳይሆን፥ እየተከፋባት፥ እያገኘባት ሳይሆን እያጣባት ያለ በመሆኑ፥ የሀገሩን ጉዳይ በሁለንተናዊ ገፅታዋ በሚገባ ስለሚያውቀው ነው፡፡ የሀገራችንን መከራ በዝርዝር ብናትትም ምፀትን ለመደጋገም ሳይሆን አዲስ ዓመት ስንቀበል አብሮን የቀጠለውን ሁኔታ መገንዘብ እንችል ዘንድ ነው፡፡

ይህ ጠባብና ጎጠኛ ቡድን አዲስ አበባ ከገባ ካለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ጀምሮ፥ በኢትዮጵያና በዜጎቿ ላይ ስለሚፈጽመው ብሔራዊ ወንጀል መጠነ-ሰፊ የሆኑ ጽሁፎች ወጥተዋል፡፡ ተነብበዋልም፡፡ በሀገር ቤትና በዓለም አቀፍ ደረጃም ለቁጥር የሚታክቱ የተቃውሞ ሰልፎች ተከናውነዋል፡፡ በግልፅና በኅቡዕ የተካሄዱት የፖለቲካና የዲፕሎማቲክ ትግሎችም የተቃውሞው አንድ አካል አንድ አምሳል የነበሩ ናቸው፡፡ በየጊዜው በአንድነት ኃይሎች በኩል ጠንካራ ኅብረት ይመጣል ተብሎ ወደ ሰባት ታላላቅ ጉባዔዎች ተጠርተው የተቃዋሚዎች ኅብረት ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም፥ የሚፈለገውን ውጤት ለማስገኘት አልቻለም፡፡ ይህ ደግሞ ገና መራራና እልህ አስጨራሽ ትግል መካሄድ የሚኖርበት መሆኑን የሚያመላክት ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ስህተትን ላለምድገም ለሚፈልግ ማንኛውም ሀገር ወዳድ ታጋይ ይህንን የትግል ታሪኩን ከተመክሮው በጥሞና እንዲያየውም የሚጋብዝ ነው፡፡

በፖለቲካ ትግል፥ የኃይሎች አሰላለፍ መለዋወጥና መበወዝ የነበረና ያለ በመሆኑ፥ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ድርጅቶችና ግለሰቦች፥ በትግሉ መራራነትም ይሁን ርዝማኔ፥ ወይም ደግሞ፥ አላፊ ጠፊ በሚሆን ጥቅማ-ጥቅም ምክንያት ጎራቸውን እየለወጡ የወያኔ ደረጃ አዳሪ ሆነዋል፡፡ "እየተሰው መታገል" የሚባለው ታሪካዊና አኩሪ ባህል እየተረሳ፥ "እየተገዙ ደጅ መጥናት" የሚባለው የወቅቱ ፈሊጥ ሆኗል፡፡ ይህ ክስተት በታሪክ የነበረ በመሆኑ ማንንም ሊያስደንቅ ባይችልም፥ ለወያኔ ግን ጊዚያዊ የሆነ የልብ ልብ ሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም እነኝህን ጋሻ-ጃግሬዎች እያሰለፈና እየበወዘ ይጫወትባቸዋል፡፡ እስከአሁን ድረስ ለአካሄዳቸው የቀልድ ምርጫዎች ሰልፍ አድማቂዎች እንዲሆኑለት ተጠቅሞባቸዋል፡፡ በዚህ በያዝነው አዲስ ዓመት ለሚያካሂደውም ተመሳሳይ የፌዝ ምርጫም እንዲያጅቡት እየኮለኮላቸው ይገኛል፡፡ "አንድ አንድ ጠብደል አለ፥ ጉተና አሳማሪ፤ ሲሄዱ በኋላ ሲመለሱ መሪ"፤ የተባለውን የቆየ ትዝብት በአሁኑ ዘመን በተግባር ለማዋል ያቆበቆቡ እንዳሉም

በኢትዮጵያ ሕዝብ በኩል ተደርሶባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የወያኔን ምርጫ አስመልክቶ ያለውን አቋምና ውሳኔ፥ በ1997ቱ ሂደት በሚገባ አሳውቋል፡፡ ይህ የዘንድሮውም የወያኔ ምርጫ ተመሳሳይ ዕድል እንደሚገጥመው ሳይታለም የተፈታ ሆኗል፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ያለው ነባራዊ ሁኔታ በገሃድ እንደሚያሳየው፥ የሀገሪቱ ጉዳዮች በሞላ፥ ከድጡ ወደ ማጡ እያሽቆለቆሉ በመሄድ ላይ መሆናቸውን ነው፡፡ በአብዛኛው ከአንድ ብሔር የፈለቁ ግለሰቦች የተሰገሰጉበት የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት እንደ ሀገሪቱ ባኅል ተቆጥሮ መላዋን ሀገርና ዜጎቿን ረግጦና ጨቁኖ ይገዛል፡፡ የሥርዓቱ ሁለንተናዊ አውታሮችና ተግባራት፥ በዚሁ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን መዳፍ ሥር ናቸው፡፡ በሀገር መከላከያ ስም የጦርና የፖሊስ ሠራዊቱ፥ የአየር ኃይሉና የፀጥታ ተቋማቱ በአንድ ብሔር አባላት የማያፈናፍን ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡ ጠቅላላ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አውታሮች፥ የገበያ እንቅስቃሴዎች፥ የገንዘብ ተቋማት፥ የፋናንስ ልውውጦች፥ ከጉልት ገበያ ጀምሮ እስከ አስመጭና ላኪ ድረስ ያሉት ተግባራት፥ ታላላቅ የንግድ መደብሮች፥ የገበያ ዋጋዎችና ቁጥጥሮች ሁሉ በዚህ ይሉኝታ-ቢስ፥ ስግብግብ በሆነ ዘረኛ ሥርዓት ቁጥጥር ሥር ወድቀዋል፡፡ የሀገሪቱ ሃይማኖታዊ ተቋማት፥ የባኅልና የታሪክ መናኸሪያዎች ሳይቀሩ የዚህ አጥፊ ሥርዓት አገልጋዮች ሆነው ተዋቅረዋል፡፡ የዚህ ሥርዓት አባላት የሀገሪቱን ሀብት ወደ ውጭ ለማሸሽ እንዲያስችላቸው ሆነው የተዋቀሩት የሀገሪቱ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት ምን ያህል የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ወደ ውጭ እንደሚያወጡ ለማወቅ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህ አልበቃ ብሏቸው፥ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግሥታት ወደ ሀገሪቱ የሚላኩትን የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታዎች ለተረጅዎች የሚመጸወቱትን ሳይቀር ወደ ራሳቸው መስመር ያዛውሩታል፡፡ የሀገሪቱ የመጓጓዣና መገናኛ፥ የህንጻና የመንገድ ሥራ ሁሉ ሳይቀር ከወያኔ አባላትና ደጋፊዎች ውጭ ለሌላ ወገን አይሰጥም፡፡ ባጭሩ፥ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊና ባኅላዊ ህይወት በሙሉ፥ በአንድ ዘረኛ አምባገነን ጥብቅ ቁጥጥር ሥር ወድቋል፡፡ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ያለው የትምህርት ሥርዓትና አሰጣጥ፥ የነገ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንዳትኖር ተብሎ የተዘጋጀና የአሁኑን ትውልድ እያጠፋ ተተኪ ኢትዮጵያ ሀገሬ ባይ ትውልድ ግን እንዳይበቅል ሆን ተብሎ የተሰናዳ እኩይ እቅድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፥ በብሔረሰብና በሃይማኖት እንዲለያይ መገደዱ ብቻ ሳይሆን፥ መሬቱም ለባዕዳን በሀራጅ ሲቸበቸብበት የግዴታ እየተመለከተ የሚኖርባት ሀገር ሆናለች፡፡ እንደ ባዕድ ቅኝ ግዛት ሁሉ፥ የሀገሪቱ ታሪካዊ ሰንደቅ ዓላማ በአደባባይ እንዳትውለበለብ በሕግ የተከለከለባት ሀገር ብትኖር፥ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በመሆኗ የዓለም ሕዝቦች በትዝብት እያዘኑላት ይገኛሉ፡፡ ጥንታዊ ታሪክ፥ አኩሪ ባኅልና ቅርስ፥ ነባር ዕምነትና የሞራል እሴት እንደሌላት ተቆጥሮ፥ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሴት ልጆቿ ወደ ባዕድ ሀገር ከሽያጭ ባላነሰ መንገድ ለዘመናዊ ባርነት እንዲሰደዱ እየተገደዱ ናቸው፡፡ ሰብዕናቸውን በሚያዋርድና ኢትዮጵያዊነታቸውንም በሚያሳፍር ተግባር

ሳይወዱ በግድ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡ ብዙዎቹ የቅርብና የሩቅ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለረዥም ዘመን ሲጠብቁት የቆዩት አመች ጊዜ ስለመጣላቸው፥ በሥልጣን እንዲወጣ የረዱትን ወያኔን ከጀርባው ተጠግተው የወንጀሉ ተባባሪዎች ሆነውለታል፡፡ ወያኔ ለሽያጭና ለአሳፋሪ ተግባር የሚልካቸውን ኢትዮጵያውያት በዕድሜ ለጋ የሆኑ ወጣቶችን እየተቀበሉ ያሻቸውን ይፈጽሙባቸዋል፡፡ እነኝህ ያልታደሉ ለጋ ወጣት ሴቶች፥ ሳይወዱ በግድ ይህን መራራ ሕይወት እንዲመሩ ሆነዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ፥ ከአለፉት ሠላሳ ዓመታት በላይ የኢትዮጵያን አምባገነን ሥርዓት በመቃወም ተሰድደው በመታገል ላይ የሚገኙትን ሀገር ወዳዶች፥ የዓለም አቀፍ የስደተኞችን ሕግ በመጣስ፥ አሳልፈው ለወያኔ ዕርድ ይሰጣሉ፡፡ ወያኔ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ በማጥፋት የነገዋን ኢትዮጵያ እንዳትኖር ለማድረግ ከሚጠቀምበት ረዥም ዕቅዱ መካከል ዋናው፥ ታሪክና ባህል የሚያውቁትንና ሕዝብንም ያስተምራሉ ብሎ የሚፈራቸውን አዛውንት፥ ሊቃውንት፥ ሀገር-ወዳድ ምሁራንና አርበኛ ታጋዮችን ማጥፋት ነው፡፡ እነዚህን የኅበረተሰብ ክፍሎች አድኖ ማጥፋት ታቀዋሚዎቼን ሁሉ ያስደነግጥልኛል ብሎ ይመኛል፡፡ ወያኔ፥ ከታሪክ የሚቀሰመውን ተመክሮ ባለመረዳቱ ሆኖ ነው እንጅ፥ አንድ ተቃዋሚ በገደለ ቁጥር አዕላፍ አርበኞች መፈልፈላቸው የሀገራችን ዜና-መዋዕል በየዘመናቱ የነበረውን ሐቅ መዝግቦታል፡፡ የዛሬይቱም ኢትዮጵያ ዕልፍ-አዕላፍ ጀግኖች ሀገር-ወዳድ አዛውንትና ምሁራን፥ አይበገሬ ታጋዮች ያሏት ብቻ ሳይሆን፥ ለመሥዋዕትም የተዘጋጁ መኖራቸውን ማወቅ ነበረበት፡፡ አጥፍቶ ለመጥፋት ካልሆነ በስተቀር፥ ጤናማ አዕምሮ ያለው ሰው የታሪክን ትምህርት ዋጋ መስጠት ይገባው ነበር፡፡ ከእባብ የእርግብ እንቁላል አይጠብቁምና፣ ይህ ባኅርይና ተግባር የአምባገነን ሥርዓት አራማጆችን ሲያልፍም አይነካቸው ብንል ሐቅ ነው፡፡ በመቃብራቸው አፋፍ ሆነው እንኳ ያ የአደቆናቸው አጋንንት ሊተዋቸው አይችልም፡፡ በሥልጣን ዘመናቸው የሚሠሩት ተግባር ሁሉ፥ ሕዝብ አክብሮ እንዲወዳቸው ሳይሆን እየናቀ እንዲጠላቸው የሚያደርግባቸው ስለሆነ፥ በመጨረሻው ሰዓት ሥልጣናቸው ከእጃቸው እያፈተለከ ሲሄድባቸው፥ ሊያደርጉት የሚችሉት፥ ያው እንደተለመደው ከሕዝብ ቁጣና ከታሪክ ለመሸሽ መሞከር ይሆናል፡፡ እየናቁ የሚጨቁኑትንና እየጠሉ የሚፈሩትን ምልዓተ-ሕዝብ የእሳተ-ገሞራ ገፅ ለመጋፈጥ ችሎታው ያንሳቸዋል፡፡ ወኔውም ይከዳቸዋል፡፡ የሕዝብን አመፅ ለማዳፈን የሚያደርጉት መፍጨርጨር ሁሉ ፋይዳ ሊኖረው የሚችል አይሆንም፡፡ ባዕዳን የጡት አባቶቻቸውና ሌሎች ተባባሪዎቻቸውም የማይበገረውን የሕዝብ ቁጣ በማየት፥ ጓዛቸውን ጠቅልለው ዘወር እንደሚሉባቸው ብዙ ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህን ሁኔታ ለማምጣትና ለማየት የሚችሉ ሁለት ኃይሎች ብቻ ናቸው፡፡ አንደኛው፥ ያው የታሪክ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በአይበገሬነቱ ፀንቶ እስከመጨረሻው የሚታገለው ኢትዮጵያዊው ኃይል ነው፡፡ ለዚህም ነው፥ አምባገነኖችና ባዕዳን ጠላቶች፥ የኢትዮጵያን ሕዝብና ኢትዮጵያዊውን ኃይል አምርረው የሚጠሉት፥ የሚፈሩትና ለማጥፋትም የሚሞክሩት፡፡

ከሞላ-ጎደል ሲታይ፥ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ ሀገሮች ለኢትዮጵያ መልካም አመለካከት እንደሌላቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች አስመስክረዋል። ይህ ደግሞ ያለምክንያት አይደለም። ከየራሳቸው ጥቅም ጋር የተያያዘ ፍላጎት ስለአላቸው ነው። የዓባይና የዋቢ ሸበሌ ወንዞች ምንጭ የሆነች አገር በወንዞቿ ተጠቅማ የልማት ተግባሮችን ብታስፋፋ ጥቅማቸው እንደተነካ ይቆጥሩታል። የነዳጅና የሌሎች ንጥረ ነገሮች ክምችት ባለቤት የሆነችው ሀገር ጠንክራና በልፅጋ ብትገኝ ለህልውናቸው አስጊ አድርገው ይገምታሉ። የምዕራብና የምሥራቅ አጎራባቾችዋ ሀገራት የኢትዮጵያ ድክመትና ክፍፍል የዘወትር ምኞታቸው ስለሆነ፥ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ማየት ሀሴትን አጎናጽፏቸዋል። ለሁለቱም ኢትዮጵያን ለማስገንጠልና ለማዳከም ለጣሩት የብሔር ድርጅቶች ሁሉ አስፈላጊውን እርዳታ ሲያደርጉ ቆይተዋል። አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን የብሔር ድርጅት አዲስ አበባ እንዲገባ አድርገው ምኞታቸውን አሳክተዋል። ኢትዮጵያም በአያሌ ዘመን ታሪኳ ከራሷ ማኅፀን የተፈጠሩ ዕኩይ ዜጎቿ፥ ከባዕዳን ጠላቶቿ ጋር ተባብረው እርሷኑ ለማጥፋት ሥልጣን ላይ ሲወጡ ለመታዘብ ቻለች። ይህም በመሆኑ ዛሬ ወያኔን ተቃውሞ የሚታገለው የኢትዮጵያ አንድነት ኃይል የአካባቢ መንቀሳቀሻ እንዳያገኝ ችግር ፈጥረውበታል። ከዚህም አልፎ ተርፎ፥ የወቅቱ የሱዳን ባለሥልጣኖች የእነርሱን ጥቅም የሚያስጠብቅላቸውን ወያኔን የሚቃወሙትን ኢትዮጵያውያን ግለሰቦች እያፈኑ ለወያኔ አሳልፈው በመስጠት ለብዙ ኢትዮጵያውያን መታረድ ምክንያት ሆነዋል። ወያኔም በአካባቢው ያለው ተንቀሳቃሽ ኃይል፥ የተዳከመ መስሎ ስለሚገምት ለጊዜውም ቢሆን ወቅታዊ ዕፎይታ እንዳገኘ ቆጥሮታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ፥ የባዕዳንን ወረራም ይሁን የሀገር ውስጥ አምባገነን ሥርዓትን ታግሎ ለመጣል የሚተማመነው በራሱ አርበኞች አይበገሬነት ለመሆኑ በተደጋጋሚ አስመስክሯል። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አርበኞችም የተለየ ባኅርይና ዕምነት የላቸውም። ዕርግጥ በአሁኑ ጊዜ፥ የዓለም አቀፉ፥ የአካባቢውና የሀገር ቤቱ ነባራዊ ሁኔታዎች በወቅታዊ መልካቸው፥ የትግላችንን ሂደት ውስብስብ ያደረጉት መስሎ ሊታይ ይችል ይሆናል። ግን የሰማኒያ ሚሊዮኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ቁርጠኝነትና የነፃነት ዕድል ሊወስኑለት አይችሉም። እንደማንኛውም የዓለም ሕዝቦች፥ የሀገራችንም ሕዝብ የራሱን የነፃነት ትግል አካሂዶ፥ የዴሞክራሲ ሥርዓት የማግኘትን ውሳኔ የሚወስነው እርሱ እራሱ ብቻ ነው። በመሆኑም፥ የሀገሩን የውስጥ ችግር፥ የራሱን ብሔራዊ ችግር፥ እራሱ በራስ ፈትቶ ለብዙ ጊዜ የሚመኘውንና ብዙም መሥዋዕት የከፈለበትን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ሀገራዊ ነፃነቱን መጎናፀፉ አይቀሬ ነው። ይህን ለማግኘት ደግሞ በምኞትና በተስፋ ብቻ እንደማይሆን አበክሮ ይገነዘበዋል። እልህ አስጨራሽ ትግልና ከባድ መሥዋዕት የሚጠይቅ መሆኑንም በሚገባ ያውቀዋል። ለነፃነት ትግል ከባድ መሥዋዕት መክፈል ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንግዳ አይሆንም። አይበገሬ ልጆቹን በጎኑ አሰልፎ የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት እንደሚያስወግድ የታሪክ ሐቅ ነው።

በኢሕአፓ መሠረታዊ ዕምነትና አቋም፥ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ከዘረኞች ሥርዓት አላቅቆ፥ የነገዋን ዴሞክራሲያዊት ሀገር ለማምጣት መካሄድ ያለበት፥ ሁለገብ ትግል ብቻ ነው። ሁለገብ ትግል ስንል ይህን እስከ አፍንጫው የታጠቀን ፀረ-ሕዝብ ዘረኛ ቡድን ማጣደፍ የሚቻለው ዘርፈ-ብዙ የሆነ የትግል ስልት ማካሄድ አስገዳጅ ነው ማለታችን ነው። ይህን ስንል፥ በፖለቲካ፥ በዲፕሎማሲ፥ በሕዝባዊ አመጽና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በትጥቅ ትግልም ጭምር ማለት ነው። የትግል ስልት ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ መብት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ከጥፋት አድኖ ከአምባገነን ሥርዓት በመላቀቅ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት፥ ምን ዓይነት ትግል ማካሄድ እንዳለበት የማንንም ፈቀድና ምክር ሊጠይቅ የሚያስፈልገው አይሆንም። የትግል ስልት የመምረጥ መብትና ውሳኔ ከማንም የማይጠብቀውና የእርሱ የራሱ አንጡራ ሀብት ብቻ በመሆኑ ለውይይት የሚቀርብ አይሆንም። በመሆኑም፥ ወቅቱ፥ ሁኔታውና፥ አካባቢው ባመቸው መጠን የተለያዩትን የትግል ስልቶችና ዘዴዎች እየተጠቀመ የመጨረሻውን ዓላማ መምታቱ አይቀሬ ነው። የጥንቱ የጧቱ የሀገራችንም ታሪክ እንዳስተማረን፥ የሀገር መሪ ሲናጥጥ፥ የከተማ ዳኛ ሲማግጥ፥ የአካባቢ ሹም ሲባልግና ሕዝብን ሲበድል፥ ፋኖ በየቦታው እያመፀ ተቃውሞውን በመግለፅ አምባገነን መሪዎችንና ባተሌ ሹሞችን ከቦታቸው ያስነሳ እንደነበረ ግልፅ ነው ።

በየጊዜው በሀገራችን የሚፈራረቁት የኢትዮጵያ አምባገነኖች የሚያመሳስላቸው አንድ አሳዛኝ ባህሪ፥ ከእነርሱ እልፈት በኋላ ለምትመጣው ኢትዮጵያና ዜጎቿ ጭራሽ የማያስቡ መሆናቸው ነው። በሥልጣን ዘመናቸው ሕዝብ በድለው፥ ሀብት መዝብረው፥ ሀገር ጎድተው ማለፋቸውን እንኳ ተገንዝበው፥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፥ ዜጎቿም እንደ ሕዝብ መቀጠል የሚገባቸው መሆኑን ጨርሶ አያስቡበትም። ከእነርሱ በኋላ ሀገሪቱን በቀጣይነት የሚመራ ተተኪ መሪ ኃይል አዘጋጅቶ ለማለፍ፥ ዕውቀቱም ሆነ ራዕዩ፥ ጊዜውም ሆነ ፍላጎቱ አይኖራቸውም። ምክንያቱም ከእነርሱ በኋላ ስለሀገሪቱ ዕጣ-ፈንታ ደንታ-ቢሶች ስለሆኑ ነው። የአፄውም ሆኑ የደርግ ሥርዓቶች የሆኑት/ያደረጉት ይህንኑ ሲሆን፥ ይልቁንም፥ ለኢትዮጵያ ያልመጣውና ስለኢትዮጵያ የማያስበው ወያኔማ ከቶውኑም፥ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሥርዓቶች የተለየ ያደርጋል ተብሎ አይጠበቅም። ከጥንስሱ እስከ ውልደቱ ዕድገቱና አሁንም እስከሚመራው ህይወቱ ድረስ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን ድምጥማጣቸውን እያጠፋ ያለ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን፥ አጥፍቷት ስለሚሄደው ሀገር የወደፊት ዕድል ያስባል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ማሰብና መጨነቅ ያለባት ስለወቅቱ ችግሯና መከራዋ፥ ጥቃቷና ውርደቷ ብቻ ሳይሆን፥ ስለወደፊቱ ዕድሏና በሕይወት መኖር አለመኖሯም ጉዳይ ሊሆን ይገባል ብለን በብርቱ እናስባለን።

ኢሕአፓ ወያኔን አምርሮ የሚታገለውም፥ የወቅቱ የሀገራችን አምባገነን ሥርዓት አራማጅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ወደ ነገይቱ ኢትዮጵያ እንዳትሸጋገር እንቅፋትና ጋሬጣ የሆነ አጥፊ ቡድን በመሆኑም ጭምር ነው። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮች ተተብትባ መያዟን

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜያት የገለጽን ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ጎላ ብለው ከሚታዩት ውስጥ ሦስቱን ብቻ ጠቁመን እናልፋለን። የመጀመሪያውና ዋናው፥ አገራችን በአንድ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን አምባገነን አገዛዝ መዳፍ ሥር መሆኗና ይኸው ቡድን እንደ ሌሎቹ አምባገነን ሥርዓቶች ዜጎቹን በመጨቆንና ሀብት በመበዝበር ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ዜጎቿ አብረው በአንድነትና በሠላም የሚኖሩበትን ዕድል ሁሉ እያጠበበ ያለ፤ ዕኩይና ከፋፋይ ቡድን መሆኑም ጭምር ነው። ሁለተኛው ደግሞ፥ የዓለም አቀፉና የአካባቢው ሁኔታዎች የኢትዮጵያን ወቅታዊ ችግሮች ያልተረዱላት ብቻ ሳይሆኑ፥ እንዲያውም ከሞላ ጎደል የወያኔ ደጋፊዎች ሆነው አገራችንን ለማዳከም ተባባሪዎች መሆናቸው ነው። በሦስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው በሁሉም ደረጃና በማንኛውም ጊዜ እንደ ደጀን ሆኖት ሊገለገልበት የሚችል፤ ተቃዋሚው ጎራ የሀገር ወዳጹን እምነቱን ሊያገኝና ለማሰባሰብ የሚችል አንድ ኃይል ጠንክሮ ያለመውጣቱ ጉዳይ ነው። ይህ ለጊዜው ሰምሮ አለመገኘቱ ደግሞ የጠቀመው ለወያኔና ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ብቻ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ አበክሮ ተረድቶታል። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ ሀገራችን ከላይ በቅደም-ተራ በተገለፁት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሳ ዙሪያው ገደል የሆነባት ሀገር ሆናለች። ከእነኝህ ጣምራ ችግሮች ለመላቀቅ የሚያስችላትን የትግል ስልትና ዘላቂ ግብ (ስትራተጂ) መንደፍ የአዲሱ ዓመት ግንባር ቀደም ዕቅድ ሊሆን ይገባል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ የበለጠ አንገብጋቢና አጣደፊ ተግባር እንደሌለው ኢትዮጵያ ሀገሬ ለምንል ሁሉ ከግልፅም ግልፅ ነው። የሕዝቡን ፍላጎትና የሚጠብቀውንም ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል ወሳኝና ቁርጠኛ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል፤ ሀገርንና ሕዝብን የመታደግ ዓላማና ግብ ብሎም ለመስዋዕት ዝግጁ ለሆኑ የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች የምናስተላለፈው የአዲስ ዓመት የትግል ጥሪ ይህንን በጥብቅ እንዲያስቡበት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንን ጥሪ በጥሞና እየተከታተለ የራሱን አዎንታዊ እርምጃ የሚወስድበትን ሁናቴ በማሰላሰል፤ ለዚህም ደግሞ የሚበጁትን የትግል መሪዎች፥ ቆራጥና ዕኑ የሆኑትን ለይቶ ከነሱና ከድርጅታቸው ዙሪያ በመሰለፍ የመሰባሰቢያ መድረኩን ለማስፋትና ለማጠናከር የራሱ አስተዋጽዖ የሚጠበቅበት ይሆናል።

ተደጋግሞ እንደተገለጸው፥ የትግላችን አልፋና ኦሜጋም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜጎቿን አንድነት ማስከበር መሆኑን በዚህ አዲስ ዓመት መግቢያ ላይ በድጋሜ የምናረጋግጠው፤ በከፋፋይ ዘረኛ ቡድን የምትማቅቀውን የዛሬይቱን ኢትዮጵያ፥ ነፃ አውጥተን፥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቷ የሚከበርባትን የነገዋን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግም ጭምር ነው። በዚህ የትግላችን ቃል-ኪዳንና ራዕይ ተመርኩዘን በዋዜማው ወቅት እንደለጽነው፥ "የመልካም አዲስ ዓመት ምኞታችን የተፋፋመ ትግል ይሁንልን!" በሚለው አጅበን እኛም የበኩላችንን አስተዋጽዖ ማበርከቱን በገባነው ቃል-ኪዳን መሠረት እንቀጥልበታለን!!